የፖስታ ድምጽ መስጫ መመሪያዎች

እባክዎን የዚህን ወረቀት ሁለቱም ጎኖች ያንብቡ

መርጫለሁ
የሚል
ተለጣፊ
FPO

1. የፖስታ ድምጽ መስጫ ወረቀት ፓኬትዎ ሁሉም ይዘቶች ያሉዎት መሆኑን **ያረጋግጡ**። የሚከተሉት ነገሮች ሊደርሱዎት ይገባል፡-

    - የእርስዎ ድምጽ መስጫ ወረቀት
    - ሚስጥራዊነትን የሚጠብቅ መያዣ
    - ቅድሚያ የተከፈለበት የድምጽ መስጫ ወረቀት መመለሻ ፖስታ
    - “መርጫለሁ” የሚል ተለጣፊ ስቲከር

ጥያቄ ካለዎት፣ ወዲያውኑ በ1-866-DCVOTES (1-866-328-6837) ያነጋግሩን (1-866-328-6837).

2. የምርጫ መመሪያውን **በጥንቃቄ ያንብቡ።**

3. **ለሁሉም ውድድሮች፡-**

    - ሰማያዊ ወይም ጥቁር ቀለም ያለው ብዕር በመጠቀም ከምርጫዎ አጠገብ ያለውን ክብ ሙሉ በሙሉ ይሙሉ።
    - በመጻፍ ድምጽ ለመስጠት፣ ክቡን ይሙሉ እና ስሙን በመጻፊያው መስመር ላይ ይጻፉ።
    - ስህተት ከሰሩ፣ ወደ 1-866-DCVOTES (1-866-328-6837) በመደወል አዲስ የድምጽ መስጫ ወረቀት ይጠይቁ።

ለእጩዎች በቅደም ተከተል ደረጃ በሚሰጥበት የምርጫ ሥርዓት (RCV) ለሚካሄዱ ምርጫዎች (በስም የተጠቀሱ 3 ወይም ከዚያ በላይ እጩዎች የሚወዳደሩባቸው ምርጫዎች)

ለRCV ውድድሮች፣ በምርጫዎ ቅደም ተከተል መሰረት እስከ አምስት (5) እጩዎችን ደረጃ ሊሰጡ ይችላሉ (1ኛ፣ 2ኛ፣ 3ኛ ወዘተ)። እስከ አምስት ለሚደርሱ እጩዎች በቅደም ተከተል ደረጃ መስጠትዎ፣ ቀደም ብለው ከፍ ያለ ደረጃ የሰጧቸውን እጩዎች አይጎዳም።

አስፈላጊ የRCV የድምጽ መስጫ ወረቀት ደንቦች፡-

- ለሁሉም እጩዎች የግድ ደረጃ መስጠት አይጠበቅብዎትም። ለአንድ እጩ ብቻ ድምጽ መስጠት እና ሌሎቹን አምዶች ባዶ መተው ይችላሉ።
- አንድን እጩ ከአንድ ጊዜ በላይ ደረጃ መስጠት የለብዎትም። (በእያንዳንዱ ረድፍ ውስጥ አንድ ክብ ብቻ ይሙሉ።)
- የደረጃ አሰጣጥን መዝለል የለብዎትም። (በተከታታይ ከአንድ በላይ ደረጃ መዝለል በዚያ ውድድር ውስጥ በሁለተኛው መዝለል ቦታ ላይ ድምጽዎ እንዳይቆጠር ያደርገዋል።)
- ለአንድ እጩ የሰጡትን የቅደም ተከተል ደረጃ ለሌላ እጩ መድገም የለብዎትም (በእያንዳንዱ ዓምድ ውስጥ ለአንድ እጩ ብቻ ኦቫሉን ያጥቁሩ።)

4. የድምጽ መስጫ ወረቀትዎን **በድጋሚ አጣጥፈው** ሚስጥራዊነትን ወደሚጠብቀው መያዣ ውስጥ ያስገቡት።

5. ሚስጥራዊነት የሚጠብቀውን መያዣ ቅድሚያ የተከፈለበት የድምጽ መስጫ ወረቀት መመለሻ ፖስታ ውስጥ **ያስገቡት።** (በድምጽ መስጫ ወረቀት መመለሻ ፖስታ ውስጥ **የእርስዎን** የምርጫ ወረቀት ብቻ ነው ማስገባት የሚቻለው። **የድምጽ መስጫ ወረቀት ከአንድ በላይ ድምጽ መስጫ ወረቀት የያዘ ከሆነ፣ ከድምጽ መስጫ ወረቀቶቹ አንዳቸውም አይቆጠሩም።**)

6. **አስፈላጊ: በድምጽ መስጫ ወረቀት መመለሻ ፖስታ ጀርባ ላይ በመራጭ ቃለ መሃላ ላይ ይፈርሙና ቀን ይጻፉ። የምርጫ ወረቀትዎ እንዲቆጠር የመራጭ ቃለ መሃላውን መፈረም አለብዎት.**

7. የድምጽ መስጫ ወረቀት መመለሻ ፖስታውን **ያሽጉ**።

8. ድምጽ የሰጡበትን የምርጫ ወረቀት ከሚከተሉት መንገዶች በአንዱ ይመልሱ፡-

    - **በፖስታ**

የድምጽ መስጫ ወረቀትዎን በአካባቢዎ ላለው የፖስታ አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ይስጡት ወይም በማንኛውም የዩናይትድ ስቴትስ ፖስታ አገልግሎት (USPS) ፖስታ ሳጥን ወይም በማንኛውም የዩናይትድ ስቴትስ ፖስታ ቤት ያስቀምጡት።

አስፈላጊ: በፖስታ የሚላኩ የምርጫ ወረቀቶች እስከ ምርጫው ቀን (ማክሰኞ፣ ኖቬምበር 3) ፖስታ ቤት መድረስ እንዲሁም ከምርጫው ቀን በኋላ እስከ 10ኛው ቀን ድረስ በምርጫ ቦርድ (BOE) መድረስ አለባቸው። በጊዜ መድረሱን ለማረጋገጥ በተቻለ ፍጥነት ድምጽዎን እንዲሰጡ እና የድምጽ መስጫ ወረቀትዎን በፖስታ እንዲልኩ እንመክራለን።

- **በማንኛውም 24 ሰዓት ደህንነቱ በተጠበቀ የምርጫ ቦርድ የፖስታ ድምጽ መስጫ ሳጥን (ከአርብ፣ ኦክቶበር 9 ጀምሮ)**

እርስዎ በDistrict of Columbia ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች በሚገኙ 55 የምርጫ ቦርድ የፖስታ የድምጽ መስጫ ወረቀት ማስገቢያ ሳጥኖች ውስጥ የድምጽ መስጫ ወረቀትዎን እስከ ምርጫ ቀን ማክሰኞ፣ ኖቬምበር 3፣ 2026 ምሽት 8:00 pm ድረስ በማንኛውም ጊዜ ማስገባት ይችላሉ።

- **(በቅድሚያ ድምጽ በሚሰጥበት ጊዜ ወይም በምርጫ ቀን ክፍት በሆነ) በማንኛውም የድምፅ መስጫ ማዕከል**

የቅድመ ድምጽ መስጫ ማዕከላት **ከሰኞ፣ ኦክቶበር 26 እስከ እሁድ፣ ኖቬምበር 1** ከ8:30 am እስከ 7:00 pm ባለው ጊዜ ውስጥ ክፍት ይሆናሉ፣ እንዲሁም የምርጫ ቀን ድምጽ መስጫ ማዕከላት **ማክሰኞ፣ ኖቬምበር 3** ከ7:00 am እስከ 8:00 pm ባለው ጊዜ ውስጥ ክፍት ይሆናሉ።

የድምፅ መስጫ ወረቀት መመለሻ ፖስታዎን በማንኛውም የድምፅ መስጫ ማዕከል ውስጥ በተጠቀሱት ቀናት እና ሰዓቶች ውስጥ በአካል በመገኘት ድምፅ መስጫ ሰልፎች ላይ ሳይጠብቁ ማስገባት ይችላሉ።

ወደ www.dcboe.org ለሚከተለው ይሁዱ፡-

- የBOE ፖስታ ድምጽ መስጫ ወረቀት ማስገቢያ ሳጥን ቦታዎች
- የቅድመ ድምጽ መስጫ ማእከል ቦታዎች
- የምርጫ ቀን የድምፅ መስጫ ማዕከል ቦታዎች
- የድምጽ መስጫ ወረቀት መከታተያ መረጃ
- ስለ ኖቬምበር 3፣ 2026 የጠቅላላ ምርጫ አጠቃላይ መረጃ እና
- በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች (FAQ)፣ እና
- ስለ ደረጃ በደረጃ ምርጫ ድምጽ አሰጣጥ (Ranked Choice Voting, RCV) መረጃ)

የመምረጥ ተደራሽነት

የአካል ጉዳተኞች እና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታቸው ውስን ለሆኑ መራጮች ተደራሽ የድምፅ መስጫ ማዕከላት፣ ከመንገድ ዳር ድምጽ መስጠት፣ የድምፅ መስጫ ምልክት ማድረጊያ መሳሪያዎች እና ሌሎችንም ጨምሮ ተደራሽ ስለሆኑ የድምፅ መስጫ አማራጮች ለማወቅ የBOE የአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ አስተባባሪን በ 202-727-5411 ያነጋግሩ።

ጥያቄዎች አሉ?

መልሱን በድረ ገጹ ላይ ማግኘት ካልቻሉ በስልክ ቁጥር 1-866-DCVOTES (1-866-328-6837) ይደውሉልን።

¿Necesita ayuda en su idioma? Llame al 1-866-DCVOTES (1-866-328-6837)
በቋንቋዎት እርዳታ ማግኘት ይሻሉ? በስልክ ቁጥር 1-866-DCVOTES (1-866-328-6837) ይደውሉ።
需要以您的语言帮助？拨打Call 1-866-DCVOTES (1-866-328-6837)
Cần sự trợ giúp ngôn ngữ của bạn? Hãy gọi 1-866-DCVOTES (1-866-328-6837)
Avez-vous besoin d'aide dans votre langue? Appelez le 1-866-DCVOTES (1-866-328-6837) 모국어로 도움이 필요하세요? 1-866-DCVOTES (1-866-328-6837) 로 전화해주세요

የኮሎምቢያ ዲስትሪክት (DISTRICT OF COLUMBIA
የምርጫ ቦርድ
WASHINGTON, DC 20003-4733

በፖስታ ወይም በኦንላይን ለተመዘገቡ ለመጀመሪያ ጊዜ መራጮች አስፈላጊ ማሳሰቢያ

መዝገቦቻችን እንደሚያመለክቱት ከዚህ ቀደም በኮሎምቢያ ዲስትሪክት በፌዴራል ምርጫዎች ላይ ድምጽ አልሰጡም እንዲሁም የመታወቂያ ሰነድዎን (ID) ቅጂ ሳያቀርቡ በመስመር ላይ ወይም በፖስታ ተመዝግበዋል።

በፌዴራል እና በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ህግ መሰረት ከሚከተሉት የመታወቂያ ሰነዶች ውስጥ አንዱን ኮፒ ከፖስታ ድምጽ መስጫ ወረቀትዎ ጋር ማቅረብ ይጠበቅብዎታል፡-

- የአሁን የሚሰራ በመንግስት ቲ-የተሰጠ ባለፎቶ መታወቂያ፤ **ወይም** የአሁን* የፍጆታ ክፍያ፣ የባንክ ሒሳብ መግለጫ፣ የመንግሥት ቼክ፣ የደመወዝ ቼክ ወይም ስምዎን እና አድራሻዎን የሚያሳይ ሌላ በመንግሥት የተሰጠ ሰነድ።

** የወጣበት፣ የሒሳብ መጠየቂያው ወይም መግለጫው ቀን ከምርጫው ዘጠና (90) ቀናት በፊት መሆን የለበትም። ከኖቬምበር 3፣ 2026 ጠቅላላ ምርጫ በፊት ያለው 90ኛው ቀን ኦገስት 5፣ 2026 ነው።*

የመታወቂያ ሰነድዎን ቅጂ በድምጽ መስጫ ወረቀቱ መመለሻ ፖስታ ውስጥ ያስቀምጡ።

ከድምጽ መስጫ ወረቀትዎ ጋር የመታወቂያ ሰነድዎን ቅጂ ካላቀረቡ፣ የድምጽ መስጫ ወረቀትዎ እንደ ልዩ (ጊዜያዊ) የድምጽ መስጫ ወረቀት ይቆጠራል፣ እናም የማንነት መታወቂያዎን ቅጂ እስከ ማክሰኞ፣ ኖቬምበር 13፣ 2026፣ 4፡45 pm ድረስ ለምርጫ ቦርድ ካላቀረቡ በስተቀር አይቆጠርም።

ይህንን መስፈርት በተመለከተ ጥያቄ ካለዎት እባክዎ በ 1-866-DCVOTES (866-328-6837) ላይ ያነጋግሩን።